ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፷፭
አዲስ አበባ ሀምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 65
ADDIS ABABA, 31st, July, 2015

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱፻፭/፪ሺ፯ ዓ.ም

የኢኮኖሚ ልማትን ለሚያግዙ የመንግሥት ፕሮጀክቶች እንዲሁም የገጠር አካባቢን ለማልማት የሚውል ብድር ከፖላንድ ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ..............ገጽ ፰ሺ፫፻፮

CONTENTS

Proclamation No. 905/2015

The Government of the Republic of Poland Credit Agreement for financing of Projects in the Modernization of the Economy and the Public Sector as well as Development of Rural Areas Ratification Proclamation................................Page 8306

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፭/፪ሺ፯

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፖላንድ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የኢኮኖሚ ልማትን ለሚያግዙ የመንግሥት ፕሮጀክቶች እንዲሁም የገጠር አካባቢን ለማልማት የሚውል ፶ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (ሃምሳ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በፖላንድ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል መጋቢት ፲፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION No.905/2015

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF POLAND

WHEREAS, an Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Poland stipulating the Government of Republic of the Poland provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit amount to 50,000,000 USD (Fifty Million United States Dollars) for financing of Projects in the Modernization of the Economy and the public Sector as well as Development of Rural areas was signed in Addis Ababa on the 20th day of March 2015;

WHEREAS ,the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Credit Agreement at its session held on the 30th day of June 2015;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

፩.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢኮኖሚ ልማትን ለሚያግዙ የመንግሥት ፕሮጀክቶች እንዲሁም የገጠር አካባቢን ለማልማት የሚውል ብድር ከፖላንድ ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፭/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Government of the Republic of Poland Credit Agreement for financing of Projects in the Modernization of the Economy and the Public Sector as well as Development of Rural Areas Ratification Proclamation No. 905/2015".

፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፖላንድ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል መጋቢት ፲፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement signed in Addis Ababa on the 20th day of March, 2015 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Poland is hereby ratified.

፫.የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፶ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (ሃምሳ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል።

3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of up to 50,000,000 USD (Fifty million United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

፬.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ ሀምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**Done at Addis Ababa, this 31st day of July, 2015**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**